የምዝገባ ቁጥር 1146

# የሰብአዊ መብቶች ጉባዔ
# HUMAN RIGHTS COUNCIL

ሰመጉ
HRCO

ሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው፡፡
HRCO stands for democracy, the rule of law *and* the respect of human rights.

ቀን ህዳር 8 2003 ዓ.ም

## የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ

## 34ኛ መደበኛ መግለጫ

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ(ሰመጉ) በዚህ 34ኛው መደበኛ መግለጫው በአገሪቱ ውስጥ የሚታየውን አጠቃላይ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ይዳስሳል፡፡በዚህ መግለጫ የተካተቱት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እስከ ህዳር 8 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ሰመጉ ባወጣቸው መግለጫዎች ውስጥ ያልተካተቱና በደል ከደረሰባቸው ግለሰቦች ከቀረቡለት አቤቱታዎችና ማመልከቻዎች እንዲሁም ከምስክሮች ቃል በመነሳት ያጣራቸውን ጥሰቶችን ያካተተ ነው፡፡
ይህ መግለጫ እስከ ህዳር 8 ቀን 2003 ዓ.ም ያለውን ሁኔታ ብቻ የሚያካትት ነው፡፡

### በመግለጫው ውስጥ የተካተቱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ዝርዝር

| ተ.ቁ | የመብቶቹ ጥሰቶች | የጉዳቱ መጠን | ገጽ |
|---|---|---|---|
| ሀ. | ሕገ ወጥ ግድያ | 2 | 2-3 |
| ለ. | ሕገወጥ እስራት | 22 | 3-6 |
| ሐ. | ህክምና መከልከል እና ማሰቃየት | 1 | 6-7 |
| መ. | አስገድዶ መድፈር | 1 | 8 |
| ሠ. | ድብደባ እና እስራት | 9 | 8-10 |
| ረ. | የደረሱበት ያልታወቀ | 2 | 10-11 |
| ሰ. | ዛቻ እና ክትትል | 6 | 11 |
| ሸ. | ከእርሻ ቦታ መፈናቀል | 1 | 11-12 |
| ቀ. | የቤት ቃጠሎ | 1 | 12-13 |
| በ. | የስራ ዋስትና ማጣት | 109 | 13 |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## ሁ. ህግ ወጥ ግድያ

ኢትዮጵያ የተቀበለችው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 እያንዳንዱ ሰው በህይወት የመኖር መብት እንዳለው ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችውና ፍጹም አስገዳጅ የሆነው የሲቪልና የፖለቲካዊ መብቶች ቃል ኪዳንም በአንቀጽ 6/1/ ላይ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር ተፈጥሮአዊ መብት እንዳለው ይደነግጋል። የኢፌዲሪ ሕገ-መንግስትም ይህንኑ በህይወት የመኖር መሰረታዊ መብት በአንቀጽ 15 ላይ ያረጋግጣል። በተጨማሪም ይህ መብት የማይደፈርና የማይገሰስ መሆኑን የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 14 ይደነግጋል። ይሁን እንጂ ይህንን ሕገ መንግስታዊና አለም አቀፋዊ አስገዳጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በሚከተሉት ግለሰቦች ላይ ግድያ ተፈጽሟል ።

1. **አቶ እንግዳወርቅ አጥናፉ ታዬ** የ40 ዓመት ጐልማሳ እና የ6 ቤተሰብ አስተዳዳሪ ሲሆኑ የሚተዳደሩት በግብርና ነው። ነዋሪነታቸውም በአማራ ክልል በምስራቅ ጐጃም ዞን ጐዛምን ወረዳ አባሊባኖስ ቀበሌ ሲሆን ይተዳደሩ የነበሩት በዚሁ ቀበሌ ባለው የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት በትርፍ ጊዜያቸው የጥበቃ ስራ እየሰሩ ነበር ። በዚህ የጥበቃ ስራ ላይ እንዳሉም ለጥበቃ ስራው እንዲገለገሉበት የተሰጣቸው ጠመንጃ በመጥፋቱ ተከሰው ጉዳዩን የተመለከተው ከፍተኛው ፍርድ ቤት የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ወስኖባቸው እንደነበር። ይህንኑ ለመፈፀም ደብረ ማርቆስ ከተማ መስከረም 20 ቀን 2002 ዓ.ም ተጉዘው እንደነበር። በቀበሌው ያሉ የፖሊስ አባላትም አቶ እንግዳ ወርቅ የት እንደሄዱ ቤተሰባቸውን ከመጠየቅም በተጨማሪ ክትትል ሲያደርጉ እንደዋሉ። አቶ እንግዳወርቅ አጥናፉ በነጋታው መስከረም 21 ቀን 2002 ዓ.ም በወረዳው ፖሊስ ጣቢያ በመገኘት የነበሩበትን ሁኔታ ቢያስረዳም በግምት ከቀኑ 11 ሰዓት አካባቢ በሚሆንበት ጊዜ በፖሊስ መኪና ተጭነው ወደሚኖሩበት ቀበሌ እንደተወሰዱ። ከዚህ በኋላም በአባሊባኖስ የቀበሌው የእስረኞ ማቆያ ውስጥ በፖሊሶችና የቀበሌ ታጣቂዎች በደረሰባቸው ከፍተኛ ድብደባ ህይወታቸው ማለፉን።ፖሊሶች ግለሰቡ የሞቱት እራሳቸውን አጥፍተው እንደሆነ ቢገልፁም አብረዋቸው በቀበሌው ውስጥ ታስረው የነበሩ ሰዎች የሟችን አስክሬን ከቀበሌው በአንዱ ቢሮ ወድቆ መስከረም 22 ቀን 2002 ዓ.ም ከጠዋቱ 5 ሰዓት አካባቢ እንደተመለከቱ። የሟች አስክሬንም በፖሊስ መኪና ተጭኖ ወደ ደብረማርቆስ ሆስፒታል ተወስዶ ከተመረመረ በኋላ ለቤተሰብ ተሰጥቶ የቀብር ስነስርአቱ መስከረም 23 ቀን 2002 ዓ.ም በቀበሌው በሚገኘው አባሊባኖስ ቤተ ክርስቲያን እንደተፈፀመ ። የምስራቅ ጎጃም ፖሊስ ባደረገበት ተፅእኖ የተነሳ ያስከሬን ምርመራ ያካሄደው ሆስፒታል ውጤቱን ለሟች ቤተሰብ ሊሰጥ እንዳልቻለ የሟች ቤተሰብ አባላት ገልፀዋል። ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናቀረበት ቀን ድረስ ገዳዮች ለፍርድ አልቀረቡም በማለት ቤተሰቦች ገልፀዋል።

2. **ወጣት አወት ወልደ ገብርኤል አስጎዶም** በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጐንደር ከተማ ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 57 ነዋሪ ሲሆን የ16 አመት ታዳጊ ወጣት እና የ6ኛ ክፍል ተማሪ ነበር።ታዳጊው ወጣት አወት ወልደ ገብርኤል ነሐሴ 14 ቀን 2002 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 2ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ከሁለት ሌሎች ጓደኞቹ ጋር በመሆን ወደየቤታቸው ቀን ውለውበት ከነበረበት ቦታ እየተመለሱ እያለ በጎንደር ከተማ ቀበሌ 02 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አብይ ቅርጫፍ በር ላይ በተለምዶ ሕብረት ት/ቤት አካባቢ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ሲደርሱ አንደኛው ጓደኛቸው ወደ ኋላ በመቅረቱ "ለምን ወደ ኋላ ትቀራለህ ና እንጂ መሽቷል እኮ!" በማለት ሲናገር የሰሜን ጎንደር ዞን ጸጥታ ዘርፍ ሀላፊ አጃቢ የሆነው ጋሻው ስጦታ የተባለ ግለሰብ እኔን ነው በሀይለ ቃል የምትናገረኝ? በማለት ሲጠይቅ አንተን አይደለም ጓደኛዬን ነው የተናገርኩት በማለት ሟች አወት ወልደ ገብርኤል ሲመልስለት የያዘውን መሳሪያ በማውጣት ደረቱ ላይ በሽጉጡ መትቶ ገድሎታል። በካርድ ቁጥር

013246/2002 ነሐሴ 14 ቀን 2002 ዓ.ም የጐንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል የሕክምና ምስክር ወረቀት እንደሚጠቁመው አወት ወልደገብርኤል የሞተው በጥይት ተመትቶ እንደሆነ እና የመታው ጥይት በሰውነቱ ውስጥ እንደቀረ ውጤቱ ያስረዳል። ገዳይ አቶ ጋሻው ስጦታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ጐንደር ዞን አስተዳደር ጸጥታ ዘርፍ ኃላፊ አጃቢ ነው።

ታዳጊ ወጣት አወት ወልደ ገብርኤልን የገደለው አቶ ጋሻው ስጦታ ሊያመልጥ ሲል በአካባቢው ሆነው የተመለከቱ ሰዎች እና ጓደኞቹ ገዳዩን ለመያዝ ሙከራ አድርገው የነበረ ቢሆንም ገዳይ ግድያ የፈጸመበትን መሳሪያ ሊይዙት ወደሞከሩት ሰዎች በማዞር አስፈራርቶ ሊያመልጥ ችሏል። ይሁንና በዚያኑ ቀን በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውሏል። በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጐንደር ከተማ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ጉዳዩን ለፍርድ ለማቅረብ ምርመራ እያካሄደ ነው።

ይሁንና የሟች ቤተሰቦች እንደገለጹት ተጠርጣሪው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ውሎ በምርመራ እየተጣራ ቢሆንም ግድያ የተፈጸመበት መሳሪያ እስከ አሁን አለመያዙንና ከምርመራ መዝገቡ ጋር አለመካተቱ በፍርድ ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል የሚል ስጋት እንዳሳደረባቸው ለሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ገልጸዋል።

## ለ. ሕገወጥ እስራት

የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 17(2) እና አለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 9 ማንኛውም ሰው በዘፈቀደ ሊያዝ አይችልም የሚለውን ድንጋጌ በመተላለፍ ከዚህ በታች ስማቸው የተገለፀው ግለሰቦች ከሕግ ውጭ ታሥረው እንግልት ደርሶባቸዋል።

### 1. የለገደንቢ ወርቅ ማዕድን ስራ ማስፋፊያን በተመለከተ የተከሰተ ችግር

በኦሮሚያ ክልል በደቡብ ኦሮሚያ በቡሌ ሆራ ወረዳ አካባቢና ሌሎች ወረዳዎች እንዲሁም በሀገረ ማሪያም ከተማና በቡሌ ሆራ ከተማ አንዳንድ ቦታዎች የሚማሩ ተማሪዎች ከህዳር 24 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የለገደንቢ ወርቅ ማዕድን ስራ ወደ አካባቢያቸው ተስፋፍቶ መቀጠሉን በተመለከተ የመብት ጥያቄዎች በማንሳታቸው ትምህርት ለአንድ ሣምንት ተቋርጦ ነበር። በዚህም ሳቢያ በአካባቢው የሚኖሩ ሰዎች እና አንድ የፖለቲካ ፓርቲ (መድረክ) አባል ሕገ ወጥ እሥርና እንግልት እንደደረሰባቸው ሰመጉ በስፍራው ሄዶ ባደረገው ማጣራት አረጋግጧል ። የድርጊቱ መንስኤም በኦሮሚያ ክልል ቡሌ ሆራ ከተማ የሚገኘው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ህዳር 24 ቀን 2002 ዓ.ም የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው መሆኑን። ተማሪዎች ትምህርት እንዲያቋርጡ መነሻ የሆነው በአካባቢው የሚገኘው የሚድሮክ ለገደንቢ የወርቅ ስራ ማዕድን ፕሮጀክት አድማሱን በማስፋት ከአካባቢው ተጨማሪ ቦታ እንደሚሰጠው በማወቃቸው ተማሪዎቹ የማዕድን ፍለጋ ስራው የአካባቢውን ገበሬዎች የሚያፈናቅል እና ስራውም በአካባቢው ሕብረተሰብ ላይ የጤና ችግር ያስከትላል በሚል ነው። የመንግስትም የፀጥታ ሀይሎች ተማሪዎችን አነሳስተዋል ያሏቸውን ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሱትን ግለሰቦች ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይዘው አስረዋቸዋል ።

## ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተይዘው የታሰሩ ሰዎች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | ዕድሜ | አድራሻ | ስራ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ በሽር ተስፋዬ | 39 | ቡሌ ሆራ ወረዳ ቡሌሆራ ከተማ | ግብርና |
| 2. | አቶ አሰፋ ቆዳ ዱለቻ | 26 | ቡሌ ሆራ ወረዳ ቡሌሆራ ከተማ | ነጋዴ |
| 3. | አቶ ዱጎ ዋቆ ዱለቻ | 26 | ቡሌ ሆራ ወረዳ ቡሌሆራ ከተማ | ነጋዴ |
| 4. | አቶ ዘነበ ዋቆ ደሴ | 48 | ቡሌ ሆራ ወረዳ ገርባ ቀበሌ | የጤና ባለሙያ |
| 5. | አቶ ሀይሉ ወርቁ በጋሻው | 47 | ቡሌ ሆራ ወረዳ ቡሌሆራ ከተማ | ግብርና |
| 6. | አቶ ጌታቸው በቀለ አየለ (ለአንድ ወር ከታሰሩ በኋላ ፍ/ቤት በነጻ አሰናብቷቸዋል) | 48 | ቡሌ ሆራ ወረዳ ቡሌሆራ ከተማ | ነጋዴ/የመድረክ አባል |

ጥር 5 ቀን 2002 ዓ.ም የክልሉ ዐቃቤ ሕግ ከላይ የተጠቀሱትን ሰዎች በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሻሸመኔ ምድብ ችሎት በሽብርተኝነት ወንጀል ከሷቸዋል፡፡ ከተከሰሱት ሰዎች መካከል 6ኛ ተከሳሽ አቶ ጌታቸው በቀለ አየለ ጥር 17 ቀን 2002 ዓ.ም በዋስ ከማረሚያ ቤት ተለቀዋል፡፡

### 2. በሞያሌ ከተማ ቤተክርስቲያን መገንባትን በተመለከተ የተከሰተ ችግር

በሞያሌ ከተማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሞያሌ ወረዳ ፊለገ ሰማዕት ቅድስት አርሴማ ቤተክርስቲያን አማኞች በኢትዮ-ኬንያ ድንበር አካባቢ በሚገኝ ቦታ ላይ ቤተክርስቲያን ለመገንባት በሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሞያሌ ወረዳ ከተማ አስተዳደርን ቦታ ጠይቀው የከተማ አስተዳደሩም ቦታውን ሰጥቷቸዋል፡፡ በ19/01/2000 ዓ.ም ለተሰጣቸው ለዚህ ቦታም ክፍያ ገቢ ደረሰኝ ቁጥር 063011 እና የከተማ ቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር 460/2000 ስለተሰጣቸው ፊለገ ሰማዕት ቅድስት አርሴማ ቤተክርስቲያን በምዕመናት የገንዘብ መዋጮ እና የጉልበት ስራ ቤተክርስቲያኑ ተገንብቶ መንፈሳዊ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንዳለ ከ23/07/2002 ዓ.ም ጀምሮ ታሽጎ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠቱን አቋርጧል፡፡በተያያዘም ሁኔታ ህገወጥ ቤተክርስቲያን ሰርታችኋል በማለት የተለያዩ የቤተክርስቲያኒቷ ምዕመኖች በተለያዩ ጊዜያት ለእስር እንደተዳረጉ እና ሌሎችም እየተፈለጉ መሆናቸውን ምዕመናኑ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡ ከታሰሩት ግለሰቦች መካከል፡-

1ኛ. አቶ ወንድሙ ገ/ህይወት
2ኛ. መሪጌታ ሠለሞን ማዕረግ
3ኛ. አቶ ታዬ ባሻው የተባሉት የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ታህሳስ 12-18 2002 ዓ.ም ተይዘው ለ6ቀን ያህል ታስረው ከቆዩ በኋላ የወረዳው ፍ/ቤት በነፃ ለቋቸዋል፡፡
4ኛ. አቶ ወንድሙ ገ/ህይወት
5ኛ. አቶ ዘርይሁን ጥበቡ



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ★ Human Rights Council ★

6ኛ. አቶ ታዬ ባሻው
7ኛ. አቶ ግርማ ተሰማ የተባሉትን የቤተክርስቲያን አባላት ከየካቲት 11-24/2002 ዓ.ም ድረስ ያለ ምንም ክስ ለ13 ቀናት ከታሰሩ በኋላ በ24/2002 ከቀኑ 8፡00 ሰዓት በዋለው ችሎት ፍርድ ቤቱ በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡

ፍርድ ቤት በነፃ ያሰናበታቸውን ግለሰቦች የሶማሌ ክልል ሞያሌ ከተማ ፖሊስ አቶ ወንድሙ ገ/ህይወት በድጋሚ በፖሊስ በቁጥጥር ስር ውሰው አብረዋቸውም ከታሰሩት ግለሰቦች መካከል 1ኛ.አቶ ትዕዛዙ ሙሉ አዳም እና 2ኛ.አቶ ብርሃኑ ታረቀኝ ከየካቲት 25 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 6 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ታስረው የክስ ቻርጅ ሳይደርሳቸው በ07/08/2002 ዓ.ም በዋስ ተለቀዋል፡፡
የምዕመናኑ ተወካዮች አቤቱታቸውን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ጽ/ቤት ያመለከቱ ሲሆን በቦረና ዞን ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት በኩል አመልክቱ በተባሉት መሰረት ወደ ቦረና ከሄዱ በኋላ ችግሩ ሳይፈታ ፡-

1ኛ. አቶ ታዬ ፈታ
2ኛ. አስር አለቃ ማሞ ካሳዬ
3ኛ. አቶ ዘሪሁን ጥበቡ
4ኛ. አቶ ካሳዬ ይልማ
5ኛ. አቶ ብርሃኑ እሸቱ ከሚያዝያ 2 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 14 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ታስረው ክስ ሳይደርሳቸው በዋስ ተለቀዋል፡፡

አቶ ወንድማገኝ አየለ ከ11/08/2002 ዓ.ም እስከ 19/08/2002 ዓ.ም ክስ ሳይቀርብባቸው በሶማሌ ክልል ሞያሌ ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ታስረው ከቆዩ በኋላ ተለቀዋል፡፡
ምዕመኑም እየደረሰባቸው ያለውን እስር እና የቤተክርስቲያን መታሸግ ለተለያዩ የክልል የአስተዳደር አካላት እና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ጽ/ቤት ብናሳውቅም ምላሽ አላገኘንም ብለዋል፡፡ ህዝበ ክርስቲያኑ በህገመንግስታዊ መብታችን በመጠቀም ሀይማኖታችንን በጋራ እና በቡድን ለማምለክ እንድንችል በህጋዊ መንገድ ማምለኪያ ቤተክርስቲያን እንድንሰራ ጠይቀን በተፈቀደልን መሰረት ቤተ ክርስቲያኗን ከሰራን በኋላ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲታሸግ በመደረጉ እና ምዕመናኑም በተለያየ ጊዜያት ለዕስር መዳረጋቸውን እና መንገላታት እንደደረሰባቸው ለሰመጉ አመልክተዋል ፡፡ በቦታው የነበሩ ምስክሮችም ይህንኑ አቆጋግጠዋል፡፡

## 3. በአማራ ክልል የደረሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች

1. **አቶ ሰለሞን ሰይፉ** የ26 አመት ወጣት ሲሆን በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 12 ነዋሪ ነው ፡፡ ቢልዲንግ ቢዝነስ ኔትዎርክ /ቢ.ቢ.ኤን/ በሚባል በክልሉ በተቋቋመ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ህገወጥ የባንክ ስራ ሰርታችኋል በሚል የወንጀል ክስ መነሻነት ለስር ተዳርገዋል፡፡ አቶ ሰለሞን የድርጅቱ ዳይሬክተር ሲሆኑ በተጠረጠሩበት ጉዳይ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፀረ ሙስና ኮሚሽን ምርመራውን ያጠናቀቀ መሆኑን ገልፆ በተጠርጣሪዎች ላይ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ይስጥበት ብሎ ጉዳዩን ይመለከት ለነበረው የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማሳሰቢያ አቅርበው እንደነበር፡፡ በዚህም ማሳሰቢያ መነሻነት ፍርድ ቤቱ በፍ/ቁ 34536 በቀን 9/2/2002 ዓ.ም ለባህር ዳር ማረሚያ ቤት ባሳለፈው ትዕዛዝ ሲከታተለው የቆየው የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ የተዘጋ መሆኑን ገልፆ ተጠርጣሪዎቹን የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽን ከማረሚያ ቤቱ እንዲረከብ ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ ይሁንና ማረሚያ ቤቱ ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም በቁጥር ባ/ማረ/አስ/692/02 በሰጠው ምላሽ በፍርድ ቤቱ በታዘዘው መሰረት የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ተጠርጣሪዎችን እንዲረከበን ደጋግመን ብንጠይቅም ሊረከበን ባለመቻሉ በስራችን ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠረብን ነው ሲል

አመልክቷል። በመሆኑም ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ተጠርጣሪው ምንም ክስ ሳይቀርብባቸው (ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 2፣3 እና 4 የተጠቀሱትን ግለሰቦች ጨምሮ) በእስር ላይ ይገኛል።

2. **አቶ ጥላሁን ደመላሽ** እድሜያቸው 37 ሲሆን ነዋሪነታቸው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 02 ነው ። ከላይ በቁጥር አንድ በተጠቀሰው ሁኔታ በ ቢውልዲንግ ቢዝነስ ኔትዎርክ /ቢ.ቢ.ኤን/ በሚል በክልሉ ውስጥ በተቋቋመ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ህገወጥ የባንክ ስራ ሰርታችኋል በሚል ወንጀል ተጠርጥረው የታሰሩ ሲሆን ምንም አይነት ክስ ሳይቀርብባቸው አሁንም በእስር ላይ ይገኛሉ ።

3. **ወ/ት ማስተዋል ያየህ ይራድ** የ19 አመት ወጣት ስትሆን ነዋሪነቷ በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 15 ነው። በቢልዲንግ ቢዝነስ ኔትዎርክ /ቢ.ቢ.ኤን/ በሚል በክልሉ ውስጥ በተቋቋመ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ህገወጥ የባንክ ስራ ሰርታችኋል በሚል ወንጀል ተጠርጥረው ከታሰሩት አንዷ ስትሆን ከላይ በተጠቀሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ክስ ሳይቀርብባት አሁንም በእስር ላይ ትገኛለች።

4. **አቶ ተካልኝ ተፈራ** የ30 አመት ጎልማሳ ሲሆኑ ነዋሪነታቸው በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 10 ነው ። ከላይ በቁጥር አንድ በተጠቀሰው ሁኔታ በቢልዲንግ ቢዝነስ ኔትዎርክ /ቢ.ቢ.ኤን/ በተሰኘ በክልሉ ውስጥ በተቋቋመ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ህገወጥ የባንክ ስራ ሰርታችኋል በሚል ወንጀል ተጠርጥረው ከታሰሩት አንዱ ሲሆኑ ክስ ሳይቀርብባቸው አሁንም በእስር ላይ ይገኛሉ ።

## ሐ. <u>ህክምና መከልከል እና ማሰቃየት</u>

### 1. ህክምና መከልከል

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት አንቀፅ 21 እና የአለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀፅ 10 በጥበቃ ስር ያሉ እና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸው በተጠበቀ ሁኔታ መያዝ እንዳለባቸው እና በተጨማሪም ከሀኪሞቻቸው ጋር የመገናኘት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል ። ይሁን እና ከዚህ ሁኔታ በሚፃረር መልኩ የሚከተለው የመብት ጥሰት ተፈፅሟል ፡

<u>**አቶ ዳዊት ይሄይስ**</u> ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ በፍ/ቤት ተወስኖባቸው በባህር ዳር ማረሚያ ቤት በህግ ታራሚነት ይገኛሉ። ግለሰቡ ባጋጠማቸው የጤና መታወክ ሳቢያ የፈለገ ህይወት ሪፈራል ሆስፒታል ለከፍተኛ ህክምና ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ሄደው እንዲታከሙ ጥቅምት 2 ቀን 2002 ዓ.ም የፃፈላቸው ቢሆንም ማረሚያ ቤቱ በህክምና ትዕዛዙ መሰረት ሄደው እንዲታከሙ ባለማድረጉ ለከፍተኛ የጤና ችግር ተዳርገዋል። ማረሚያ ቤቱ በተደጋጋሚ የፈጸመባቸውን ይህንን የመብት ጥሰት በተመለከተ በተደጋጋሚ ለክልሉ ፍትህ ቢሮ አቤቱታቸውን ቢያቀርቡም ምላሽ አለማግኘታቸውን ለሰመጉ ገልፀዋል።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

## 2. <u>ማስቃየት</u>

ማሰቃየት እና ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው ሰብአዊነት የጎደላቸውን፣አዋራጅ የሆኑ ምርመራዎችን ለማስቀረት የተደረገውን አለማቀፍ ስምምነት እና ኢትዮጵያ ያፀደቀችው እንዲሁም የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 19 ንኡስ ቁጥር 5 የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በሀይል ተገደው ማስረጃ እንዳይሰበሰብባቸው የሚከለክለውን አንቀጽ በመተላለፍ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ግለሰቦች ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተፈፅሞባቸዋል፡፡

2.1 **ታዳጊ ወጣት ታዴ ወርቁ** የ15 ዓመት ወጣት እና በአማራ ክልል ምዕራብ ጐጃም ዞን ጐዛምን ወረዳ አባ ሊባኖስ ቀበሌ ነዋሪ ሲሆን ከላይ በፊደል 'ሀ' የተገለጹት ሟች አቶ እንግዳወርቅ አጥናፉ ጋር ይኖር ስለነበር ጠፋ ከተባለው መሳሪያ ጋር በተገናኘ መስከረም 20 ቀን 2002 ዓ.ም ከጠዋቱ 12 ሰዓት መንገድ ላይ እንዳለ በሁለት የቀበሌው ፖሊሶች ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ተይዞ የታሠረ ሲሆን በታሠረበት የቀበሌው እስር ቤት በመስከረም 20 ከምሽቱ 12 ሰዓት እና መስከረም 21 ቀን 2002ዓ.ም መሣሪያው የት ነው እየተባለ ከፍተኛ ድብደባ እና ማሰቃየት እንደተፈፀመበት ፡፡ በዚህም ድብደባ ሳቢያ እግሮቹ መገጣጠሚያ ላይ ከባድ ጉዳት በመድረሱ መራመድ እንዳይችል አድርጐት እንደነበር ገልጿል፡፡

2.2 **አቶ አበበ ይቴ** አርሶ አደርና የ45 ዓመት ጐልማሳ ሲሆኑ በአማራ ክልል ምዕራብ ጐጃም ዞን ጐዛምን ወረዳ አባ ሊባኖስ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው፡፡ ከላይ በፊደል ተራ 'ሀ' በተጠቀሰው መሳሪያ ሰርቀሃል አውጣ በሚል መስከረም 20 ቀን 2002 ዓ.ም ከጠዋቱ 12 ሰዓት ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከተኙበት ከቤታቸው ተይዘው የታሰሩ መሆኑን ቀኑን ሙሉ ምንም አይነት ምግብ እንዳያገኙ እና ሽንት ቤት እንዳይሄዱ ተከልክለው የዋሉ መሆኑን እና ከምሽቱ 5 ሰዓት ሲሆን ከታሰሩበት ክፍል እየተጠሩ በተለምዶ የፊጥኝ እስር በመባል በሚታወቀው ሁኔታ እጃቸውን ታስረው በፖሊስ ዱላ መላ ሰውነታቸውን መደብደባቸውን በዚህም ሳቢያ እጃቸውና እግራቸው እንደተጎዳ አመልክተዋል ፡፡

2.3 **አቶ አለምነህ አንቴ** ገበያ የ28 አመት ወጣት አርሶአደር ሲሆን ነዋሪነቱ በአማራ ክልል ምዕራብ ጐጃም ዞን ጐዛምን ወረዳ አባሊባኖስ ቀበሌ ነው ከላይ በተራ ቁጥር 2.2 በተገለጸው ሁኔታ ጠፋ የተባለውን መሳሪያ ሰርቀሀል በሚል ምክንያት መስከረም 20 እና 21 2002 ዓ.ም ታስሮ በግምት ከምሽቱ 5 ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ከታሠረበት እየተጠራ እጆቹን በተለምዶ የፊጥኝ እስር እየተባለ በሚታወቀው ማሰቃያ አይነት ታስሮ ከፍተኛ ድብደባ እንደተፈፀመበትና ወደ ታሰረበት ክፍል መመለስ እንኳን አቅቶት የነበረ መሆኑን እና እስከ አሁን ድረስም የመራመድ ችግር እንዳለበት ለሰመጉ አመልክቷል፡፡

2.4 **አቶ ልንገርህ እጅጉ** የ22 አመት ወጣትና አርሶ አደር ሲሆን ከላይ በተገለጸው ቦታና ጠፋ በተባለው መሳሪያ ሳቢያ ሰርቀሀል በሚል ምክንያት መስከረም 21 ቀነ 2002 ዓ.ም ከጠዋቱ 2 ሰዓት ከቤቱ ተወስዶ ታስሮ ከዋለ በኋላ ከምሽቱ 5ሰዓት ሲሆን ከታሰረበት ተወስዶ ሲደበድቡት ሲሉ አራቱ ፖሊሶች እርስ በርስ በመጣላታቸው ድብደባ ሳይፈጸምበት መቅረቱን ይሁንና ከፍተኛ መረበሽ እና ጭንቀት እንደፈጠረበት ገልጿል ፡፡

## መ. አስገድዶ መድፈር

**ተማሪ እናት ፈንቴ ቢሹ** እድሜዋ 18 በአማራ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ጐንደር ፋርጣ ወረዳ ቀበሌ 03 ነዋሪ ነች ። በወረዳው የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ሆና እያገለገለች ሳለ ግንቦት 25 ቀን 2001 ዓ.ም ከምሽቱ 5 ሰዓት አካባቢ የቀበሌው ሊቀ መንበር ጎቤ ክንዴ፣ የሚሊሻ ኃላፊ አበረ ደመላሽ፣ ሚሊሻ መላክ ጀንበር እና ሚሊሻ ቢተው በላይ እናት ፈንቴ ተከራይታ ወደምትኖርበት ቤት በመምጣት በሩን እንድትከፍት ሲያስገድዷት ፈቃደኛ ባለመሆኗ የቀበሌው ሚሊሻ ኃላፊ አበረ ደመላሽ የቤቱን በር ሠብሮ ሲገባ መቻሉንና ተማሪ እናት ፈንቴ በተከፈተው በር ለማምለጥ በምትሞክርበት ጊዜ ሚሊሻ መላክ ጀንበር በያዘው ክላሽ ሠደፍ በመምታት እጇጅ ከጣላት በኋላ አበረ ደመላሽ እቤት አስገብቶ ተበዳይ እናት ፈንቴን በጩቤ በማስፈራራት ክብረንፅህናዋን ከገሠሠ በኋላ ከውጪ የሚጠብቁ የነበሩትን ግብረአበሮቹን! "ሂዱ ገብቻለሁ" በማለት እርሱ እስከንጋት ድረስ በተደጋጋሚ አስገድዶ የግብረ ስጋ ግንኙነት ሲፈፅምባት ከቆየ በኋላ ከንጋቱ 11 ሰዓት ሲሆን ወጥቶ መሄዱን በዚህም ምክንያት እናት ፈንቴ ስለፀነሠች ነሐሴ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ብር 1135 (አንድ ሺህ አንድ መቶ ሠላሳ አምስት) በመክፈል ባህር ዳር ከተማ ቤዛ ክሊኒክ የ3 ወር ፅንስ እንዲቋረጥ እንዳደረገች ተገልፆዋ ።

እናት ፈንቴ እነዚህን የመብት ጥሰት የፈፀሙባትን ሰዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ለወረዳው ፖሊስ አቤቱታ ብታቀርብም ይህ መግለጫ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የተወሰደ እርምጃ የለም ።

## ሠ. ድብደባ እና እስራት

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 18/1/ ላይ ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢሰብአዊ ከቸነና ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው። በማለት የደነገገውን እና በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 5 ላይ የተደነገገውን በመጣስ በሚከተሉት ግለሰቦች ላይ ድብደባና የማስቃየት ተግባር ተፈጽሟል።

1. **አቶ ልየው መኮንን ውቤ** የ40 ዓመት ጐልማሳ፣ በአማራ ክልል ምስራቅ ጐጃም ዞን ስናን ወረዳ ሽዋ ኪዳነምህረት ቀበሌ ነዋሪና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ አባል ናቸው። በግብርና የሚተዳደሩ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የቀበሌው ደን ጠባቂ ናቸው ። የቀበሌው የጸጥታ ኃላፊ ደኑን በሕገወጥ መንገድ በመቁረጣቸው እና በዚህም ሳቢያ መስከረም 21 ቀን 2002 ዓ.ም ለቀበሌው የመሬት ዴስክ አቤቱታ በማቅረባቸው አቤቱታው የቀረበበት ኃላፊና ሁለት ፖሊሶች በመሆን "አንተን ብሎ ከሳሽ" በማለት በመሳሪያ አፈሙዝና በዱላ የደበደቧቸው ሲሆን ድብደባውን መቋቋም ባለመቻላቸው ከድብደባው ለማምለጥ ሲሮጡ ደብዳቢዎቹ አንድ ጥይት የተኮሱባቸው ቢሆንም ጥይቱ ሳይመታቸው ማምለጣቸውን፣ ይህን የደረሰባቸውን የመብት ጥሰት ለስናን ወረዳ ፅ/ቤት አመልክተው እንዲጣራላቸው ቀበሌው ታዞ የነበረ ቢሆንም በሽዋ ኪዳነምህረት ቀበሌ የሚገኙ ፖሊሶች ከወረዳው የታዘዘውን ደብዳቤ ቀዳደው በመጣል አቤቱታ አቅራቢውን መስከረም 23 ቀን 2002 ዓ.ም በድጋሚ እንዳሰሩዋቸው፡ ከለሊቱ 6 ሰዓት ሲሆንም ከቀበሌው እስር ቤት በማውጣት ድብደባ እንደተፈፀመባቸውና በድብደባውም ፊታቸው፣ እግራቸውና በአጠቃላይ መላ ሰውነታቸው ላይ ቁስለት እንደደረሰባቸው። ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የመብት ጥሰት በፈጸሙት ሰዎች ላይ የተወሰደ ሕጋዊ እርምጃ አለመኖሩ ተገልጿል።

2. **አቶ ቸሬ ዋለልኝ** የ40 ዓመት ጐልማሳና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ጐጃም ዞን ስናን ወረዳ ሽዋ ኪዳነ ምህረት ቀበሌ ነዋሪ ሲሆኑ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ አባል መሆናቸውን። መስከረም 22 ቀን 2002

ዓ.ም ከጠዋቱ 2 ሰዓት ሲሆን ለአቤቱታ ወደ ቀበሌው አስተዳደር 9 ሰዎች ሆነው መሄዳቸውን በዚህ ጊዜም ከዘጠኙ አቤቱታ አቅራቢዎች መካከል 6 አቤቱታ አቅራቢዎች ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ በማድረግ 1ኛ. አቶ ቸሬ ዋለልኝን፣ 2ኛ. አቶ እርቅይሁን ካሴን፣ 3ኛ. አበባይ ጀርጋን 'ከደብረ ማርቆስ የመኢአድ የአባልነት ቅጽ ይዛችሁ በመምጣት አባል ትመለምላላችሁ' በማለት ፖሊሶች በቀበሌው እስር ቤት እንዳሰሯቸውና ከለሊቱ 6 ሰዓት ሲሆን እርስ በርስ በገመድ አጠላልፎ ሶስቱንም በማሠር ሻማ ማጠቢያ በተባለ ቦታ በመውሰድ ከግንድ ጋር እንዲታሰሩ ካደረጉ በኋላ እንደገና እያንዳንዳቸውን በገመድ በማሰር በመሳሪያ ሰደፍና እንዲሁም ከነበሩበት ጫካ ዱላ በመቁረጥ ድብደባ ካደረሱባቸው በኋላ በነጋታው ማለትም መስከረም 22 ቀን 2002 ዓ.ም እንደለቀቁዋቸው ገልጸዋል፡፡

3. **አቶ እርቅይሁን ካሴ ባይለየኝ** የ35 አመት ጉልማሳ እና ነዋሪነታቸው በአማራ ክልል ብሔራዊ መንግስት ምስራቅ ጐጃም ዞን ስናን ወረዳ ሸዋ ኪዳነ ምህረት ቀበሌ ነው ፡፡ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ አባል ሲሆኑ ከላይ በተራ ቁጥር 2 በተገለጸው ሁኔታ ተደብድበው ጉዳት እንደደረሰባቸውና በነጋታው መስከረም 22 ቀን 2002 ዓ.ም እንደተለቀቁ ገልጸዋል ፡፡
4. **አቶ አበባይ ጀርጋ አንዱአለም** የ20 አመት ወጣት እና ነዋሪነቱ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምስራቅ ጐጃም ዞን ስናን ወረዳ ሸዋ ኪዳነ ምህረት ቀበሌ ነው፡፡ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ አባል ነው፡፡ ከላይ በተራ ቁጥር 2 ከተገለጸው ከአቶ ቸሬ ዋለልኝ ጋር በተገለጸው ሁኔታ ድብደባ ተፈጽሞበት ጉዳት የደረሰበት ሲሆን ከዚሁ በተጨማሪ መስከረም 23 ቀን 2002 ዓ.ም ታስሮ በተራ ቁጥር 1 በተገለጸው ሁኔታ ከአቶ ልየው መኮንን ጋር ለሁለተኛ ጊዜ ድብደባ እንደተፈጸመበት ገልጿል፡፡

   ሰመጉ እንዳጣራውም አራቱም ግለሰቦች ከእስር የተፈቱት የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ፓርቲ አባልነታቸውን ለመተው መሳሪያ እየጨበጡ ከማሉ በኋላ መሆኑ ታውቋል፡፡
5. **አቶ ፀሐይ ቦጋለ አከላቴ** ዕድሜያቸው 33 አመት ሲሆን ነዋሪነታቸው ደግሞ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 03 ነበር፡፡ ይሁንና ለስራ ጉዳይ በንግድ ስራ ይተዳደሩ ወደ ነበሩት እህታቸው ወ/ሪት አስቴር ቦጋለጋ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጉባ ወረዳ አረንጃ ቀበሌ በመሄድ የሆቴል ስራ በመስራት ላይ እያሉ ፍየሎቻችሁ እህል በልተዋል በሚል ምክንያት ጥቅምት 22 ቀን 2002 ዓ.ም ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ከቤታቸው ድረስ በመምጣት በመጀመሪያ የሚበሉበትን ትሪ በእግራቸው ከመቱ በኋላ አራት የልዩ ሐይል ፖሊሶች፣ ሶስት የወረዳው ፖሊሶች እና ሁለት የጸጥታ ዘርፍ ሐላፊዎች በመሆን በያዙት ዱላ እና የጠመንጃ ሠደፍ፣ እንዲሁም መሬት ላይ ካስተኛቸው በኋላ በኤሌክትሪክ የሽቦ ገመድ መላ ሰውነታቸውን የደበደቧቸው ሲሆን ከዚያም በኋላ ፀጉራቸውን ላጭተውና ሁለት እጃቸውን የፊጥኝ በማሰር ከመኖሪያቸው 62 ኪ.ሜትር ርቀት ወደሚገኘው ማንኩሽ ፖሊስ ጣቢያ ወስደው እንዳሰሩዋቸው አስረድተዋል፡፡ በነጋታው ጥቅምት 23 ቀን 2002 ዓ.ም በዐቃቤ ሕግ ትዕዛዝ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ክስም ሳይመሰረትባቸው መለቀቃቸውን ገልጸዋል ፡፡
6. **ወ/ት አስቴር ቦጋለ አካላቴ** የ25 አመት ወጣትና ነዋሪነቷ በአማራ ክልል ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 03 ነው፡፡ ከምትኖርበት ባሕር ዳር ከተማ ለንግድ ስራ ወደ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጉባ ወረዳ አረንጃ ቀበሌ በመሄድ በሆቴል ስራ ላይ ተሰማርታለች፡፡ ከላይ በተራ ቁጥር 1 በተመለከተው ሁኔታ ወንድሟን ፀሐይ ቦጋለ አካላቴን ሲደበድቡት በሕግ አምላክ ብላ በመጮኂ የፀጥታ

Human Rights Council

ሀይሎች በያዙት የፖሊስ ዱላና የጠመንጃ ሠደፍ ድብደባ ያደረሱባት መሆኑንና ከዚህም በላይ ሆዷ ላይ በመመታቷ ከፍተኛ ህመም እንደደረሰባት አመልክታለች ፡፡

ተጐጂዎች ክስ የመሰረቱ ቢሆንም በጸጥታ ሀይሎች ላይ የተወሰደ ምንም አይነት ሕጋዊ እርምጃ እንደሌለ አሳውቀዋል ፡፡

**7.** ከታች በሰንጠረዡ ስማቸው የተገለጹት ግለሰቦች የሚኖሩት በምዕራብ ጎጃም ዞን ባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 16 ልዩ ስሙ ደቂ የሚባል አካባቢ ሲሆን የአንድ ቤተሰብ አባላት ናቸው፡፡ በወንጀል የምንፈልገውን የደበቃችሁትን ልጃችሁን ካላመጣችሁ ተብለው ድብደባ እና እስር እንደተፈጸመባቸው አመልክተዋል ፡፡

| | ስም | እድሜ | ስራ | የደረሰው ጉዳት | የታሰሩበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወ/ሮ እመቤት ሙጩ አለሙ | 21 | የቀን ሰራተኛ | የቀኝ እግር ታፋቸው ላይ እብጠት (ስምበር) | --- |
| 2 | ወ/ሮ አበዝ አታሎ | 45 | ገበሬ | በመቀመጫቸውና በቀኝ እግራቸው ላይ እብጠት | ከሰኔ 9 ቀን 2001 እስከ ሰኔ 10 (ከቀኑ 6 ሰዓት ድረስ) 2001 |
| 3 | አቶ ሙጩ አለሙ | 60 | ገበሬ | በእግራቸው ጭን ላይ እብጠትና ቁስለት | ከሰኔ 9 ቀን 2001 እስከ ሰኔ 10 (ከቀኑ 6 ሰዓት ድረስ) 2001 ዓ.ም |

ከላይ የተጠቀሱትን ግለሰቦች ሰኔ 9 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 11:30 አካባቢ ላይ ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት የባህር ዳር 6ኛ ፖሊስ ጣቢያ አባል የሆነው ምክትል ኢንስፔክተር ደጉ እንሻው ግለሰቦቹ መኖሪያ ቤት ድረስ በመሄድ በእርግጫ እና በጥፊ እንዲሁም የአቶ ሙጩን ዱላ በመንጠቅ ከላይ በተጠቀሱት የቤተሰብ አባላት ላይ በድብደባ ጉዳት እንዳደረሰባቸውና ድብደባውን ከፈፀመባቸው በኋላ ከላይ በሰንጠረዡ የተጠቀሱት ግለሰቦች ላይ ክስ ሳይመሰርትባቸው እና ፍርድ ቤትም ሳይቀርቡ ሰኔ 10 ቀን 2001 ዓ.ም ከቀኑ 6 ሰዓት ድረስ ታስረው የተለቀቁ መሆኑን ለሰመጉ አመልክተዋል ፡፡

## ረ. <u>የደረሱበት ያልታወቀ</u>

1. **ወጣት ቢኒያም በላይ** ነዋሪነቱ በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክ/ከተማ ውስጥ የሆነ ተማሪ እና የ25 አመት ወጣት ነው፡፡ የቢኒያም ወላጅ እናት የሆኑት ወ/ሮ ሽታዬ ተ/ማርያም ለሰመጉ እንዳመለከቱት ልጃቸው በምርጫ 97 ታዛቢ እንደነበር እና የሰመጉ አባል መሆኑን ገልፀው በተለያዩ ቦታዎች እና ሰዓት ማንነታቸውን በማያውቃቸው የፀጥታ ሀይሎች ዛቻ እና ክትትል ይደረግበት እንደነበር፣ በዚህም ምክንያት ቤተሰብ ይጨነቅ እንደነበርና በጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም ከቤት እንደወጣ ባለመመለሱ ልጃቸውን ለማግኘት ብዙ ጥረቶች ቢያደርጉም እስካሁን ድረስ የሚገኝበትን ሁኔታ ባለማወቃቸው ከፍተኛ ስጋት ላይ እንደሚገኙ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

2. **ወጣት ተመስገን ተስፋዬ** ነዋሪነቱ በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክ/ከተማ ውስጥ ሲሆን በግል ስራ የሚተዳደር ግለሰብ ነው ። ተመስገን ተስፋዬ ምርጫ 97ን ተከትሎ በተከሰተው ግጭት "አንተም ተባባሪ ነህ ግጭት ቀስቃሽ ነህ" ተብሎ ሰንዳፋ ታስሮ እንደነበር እና ከዚያም ከተፈታ በኋላ ማንነታቸውን በማያውቃቸው የፀጥታ ሀይሎች ክትትል እና ዛቻ ይደረግበት እንደነበር፣ በዚህም ምክንያት ከፍተኛ ስጋት ላይ ይገኝ እንደነበር፣ በመጨረሻም ግንቦት 20 ቀን 1998 ዓ.ም ይኖርበት ወደነበረበት ቤት የማያውቃቸው ግለሰቦች ሲመጡበት ሸሽቶ ወጥቶ እስከዛሬ ድረስ አለመመለሱን ቤተሰቡም በፖሊስ ጣቢያ፣ በሆስፒታልና በተለያየ ቦታ ቢያፈላልጉትም ሊያገኙት ስላልቻሉ ስጋት ላይ መውደቃቸውን ወላጅ አባቱ አቶ ተስፋዬ መንገሻ ለሰመጉ አመልክተዋል።

## ሰ. ዛቻና ክትትል

1. **አቶ ሀብታሙ ግርማ** ነዋሪነቱ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሲሆን የ30 አመት ወጣት፣ ባለትዳር እና የልጅ አባት ነው ። አቶ ሀብታሙ ግርማ የሰመጉ መደበኛ አባል ሲሆን በተለያዩ ድህረ ገጾች እና ጋዜጦች ላይ ስለ መልካም አስተዳደር እና ዴሞክራሲ እንዲሁም ሰብአዊ መብቶች በመፃፍ ይታወቃል ። በዚህም ምክንያት ማንነታቸውን የማያውቃቸው የፀጥታ ሀይሎች "አንተ የመንግስት ተቃዋሚ እና የግንቦት 7 አባል ነህ በተለያየ ፅሑፎችም ፀረ-መንግስት አቋም ነው ያለህ" በማለት የተለያዩ ቦታዎች ላይ እየጠበቁ እየዛቱበት እና በስልክም እየደወሉ እያስፈራሩት እንደሆነና ከፍተኛ ስጋትና ፍርሃት ላይ እንደሚገኝ ለሰመጉ አመልክቷል ።

2. "በ2001 ዓ.ም በቅዱስ ሲኖዶስ ውስጥ የተከሰተውን የተዛባ አሰራር እንዲስተካከል"በመጠየቃችን ብቻ ተደብድበናል እንዲሁም ከስራ /ከአገልግሎታችን/ ተባረናል፤ በዚህም ምክንያት በከፍተኛ ችግር ላይ ወድቀን እንገኛለን በማለት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በማገልገል ላይ የነበሩ ከዚህ በታች የተጠቀሱ የቤተክርስቲያኗ ሰራተኞች ለሰመጉ አመልክተዋል ስማቸውም ከዚህ በታች እንደሚከተለው ነው እነርሱም፣
    1. አባ ኤልያስ እምሩ
    2. ቀሲስ ገረመው አደመ
    3. አባ ኃ/ገብርኤል ደነቀ
    4. አባ ገ/አምላክ አበበ
    5. አባ ሐ/ማርያም ቦጋለ የተባሉት ሲሆኑ

    የደረሰባቸውንም በደል ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቢያሳውቁም ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጣቸው እንዳጣ እና ጥያቄያቸውንም እንዲያቆሙ በፀጥታ ሀይሎች ዛቻና ክትትል እየተደረገብን ነው ሲሉ ለሰመጉ በአካል መጥተው አመልክተዋል።

## ሸ. ከእርሻ ቦታ መፈናቀል

**አቶ ሀይሉ ወንዴ እምሩ** የ45 አመት ጐልማሳና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ጐጃም ዞን በባሕር ዳር ዙሪያ ወረዳ የነሳ ቀበሌ ልዩ ስሙ አጫበር ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ነዋሪ ነበሩ። በግንቦት ወር 1999ዓ.ም በቀበሌው የሚኖሩ ከ600 አባወራዎች በላይ የእርሻ መሬታቸው ለአበባ እርሻ ተከልሎ ሲሰጥና አቶ ሀይሉ ወንዴም ከእርሻ መሬታቸው እንዲነሱ

ሲደረግ ነገር ግን ካሳም ሆነ ተተኪ የእርሻ መሬት እንዳልተሰጣቸው በመሆኑም ለባሕር ዳር ዙሪያ አስተዳደር ጽ/ቤት አቤቱታቸውን በተደጋጋሚ ማቅረባቸውን ሆኖም ካሳም ሆነ ተተኪ የእርሻ መሬት ያልተሰጣቸው በመሆኑ ከ6 ቤተሰቦቻቸው ጋር ለከፍተኛ ችግር መጋለጣቸውን ለሰመጉ አመልክተዋል ፡፡

## ቀ. የቤት ቃጠሎ

**አቶ ሁሴን ቱሴ** በደቡብ ብሔር ብሄረሰቦች ሕዝቦች ክልል በሀዋሳ ከተማ በታቦር ክፍለ ከተማ በፏራ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው ፡፡ ቀደም ሲል ይህ ቦታ በሲዳማ ዞን በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ አላሞራ ቀበሌ ገበሬ ማህበር የነበረ ሲሆን አቶ ሁሴንም በእርሻ እየተዳደሩ፤ግብር እየከፈሉ ሁለት ክፍል ሣር ቤት ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት ከተማው እየሠፋ ሲመጣ በሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ የነበረው አላሞራ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ወደ ሀዋሳ ከተማ እንዲጠቃለል ተደርጎ ታቦር ክፍለ ከተማ ፏራ ቀበሌ ተብሎ መሬቱ ተሸንሽኖ ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲሠጥ ተደርጓል፡፡
አቶ ሁሴን ቱሴም ከገበሬ ማህበር አንስቶ ሲኖሩበት የነበረውን ሁለት ክፍል ሣር ቤት እንዲለቁ ለእሳቸውም ሌላ ምትክ ቦታ እንዲሚሰጣቸው ተገልጾላቸው በመጠባበቅ ላይ ነበሩ፡፡ በኋላም ምትክ ቦታ ሣይሠጣቸው ከቦታው እንዲነሱ ሲጠየቁ በሕጉ መሠረት ምትክ ቦታ ይሠጠኝና እለቃለሁ በማለት ከከተማው ማዘጋጃ ቤት ጋር ሲወዛገቡ እንደቆዩ፣ ቦታው ለእኛ ተሰጥቶናል የሚሉ ግለሰቦችም አንደኛ ተከሳሽ የከተማውን ማዘጋጃ ቤት ፣ሁለተኛ ተከሳሽ አቶ ሁሴን ቱሴን አድርገው በመክሰስ ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን አቶ ሁሴን ቱሴ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር ሣይገቡ ብይን ሰጥቷል፡፡
በ12/06/2002 ዓ.ም በቀኑ 8:00 ሰዓት ላይ የታቦር ክፍለ ከተማ ፓሊስ ኢንስፔክተር ሚሊዮን አምቼ እና የታቦር ክፍለ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሰራተኛ የሆኑት አቶ አስራት ግንጃሞ አቶ ሁሴን ቱሴን ከቤት በመጥራት እጅ ወደ ላይ በማለት አቶ ሁሴንን እየገፈተሩና እያንገላቱ በመኪና ጭነው ወስደው አስረዋቸዋል፡፡ በወቅቱ በቦታው ላይ ከ 12 በላይ ፖሊሶች የነበሩ ሲሆን ቤቱን እንዲያቃጥሉ የፖሊስ ኢንስፔክተር ሚሊዮን አማቼ ትእዛዝ በመስጠት አቶ አስራት ግንጃሞና ቦታው ተሰጥቶኛል የሚለው ግለሰብ አቶ ገዛኸኝ ጋሜ ቤቱን በክብሪት ለኩሰው እንዳቃጠሉ ቤቱም ተቃጥሎ እስከሚያልቅ ድረስ አቶ ሁሴን ቱሴን አስረው አቆይተው ከምሽቱ 1:00 ሰዓት ላይ እንደለቀቁዋቸው በቃጠሎው የወደመው የንብረት ዝርዝር
ምትክ ቦታ ቢሰጣቸው ቤት ለመስራት ያዘጋጁቸውን እና የመኖሪያ ቤት እቃዎችን ያካተተ መሆኑን አቶ ሁሴን እንደሚከተለው አቅርበውታል ፡፡

1. ሲሚንቶ 100 ኩንታል
2. ቆርቆሮ 80 ቅጠል

3. ካዲስኮ ቀለም 50 ጋሎን
4. ቁመቱ ባለ 3 ሜትር እና ስፋ 30 ሣ.ሜ የሆነ 10 ጣውላ
5. 100 ኩንታል በቆሎ
6. 2 አልጋ ከነ እስፖንጅ ፍራሽ፤ብርድልብስ
7. 2 የመሬት ሳጥን እስከነ የቤተሠቡ ሙሉ ልብስ
8. 100.000 ብር በአንደኛው ሣጥን ውስጥ የነበረ
9. ጠቅላላ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች

## በ. የስራ ዋስትና ማጣት

በደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በከምባታ ጠምባሮ ዞን ጠምባሮ ወረዳ ግንቦት 4 ቀን 2002 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ 109 መምህራን ብር 841.00 (ስምንት መቶ አርባ አንድ) በወር ደመወዝ እያገኙ እንዲሰሩ በጀማሪ መምህርነት የተቀጠሩ ሲሆን በዚሁ መሰረት መምህራኑ በየተመደቡበት ት/ቤቶች በመገኘት ወሩን በሙሉ የማስተማር አገልግሎት ከሰጡ በኂላ ወሩ ሲጠናቀቅ ማለትም ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም ለደመወዝ ጥያቄ ወደ ት/ቤቶች ጽ/ቤት ሲመጡ ቅጥሩ ተሰርዟል፣ ደመወዝም አይከፈላችሁም፣ ከአሁን በኂላ ስራ አቁሙ ይባላሉ ። መምህራኑም ከዚህ ድርጊቱ በኂላ አቤቱታቸውን ለተለያዩ የመንግስት አካላት ማቅረባቸውን ጉዳዩን በተመለከተ የወረዳው መምህራን ማህበር ለዞኑ ትምህርት መምሪያና ለክልሉ ትምህርት ቢሮ በጻፈው ደብዳቤ የቅጥሩ መሰረዝ ህገ ወጥ መሆኑን መግለጹን ከዚህም በተጨማሪ የደቡብ ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ትምህርት ቢሮም ሰኔ 8 ቀን 2002 ዓ.ም በቁጥር 002/1875 ለ19/35 ለከምባታ ጠምባሮ ዞን ትምህርት መምሪያ በጻፈው ደብዳቤ የመምህራኑ ቅጥር መሰረዝ አግባብነትና ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልፆ የትምህርት መምሪያ ጉዳዩን አጣርቶ ለመምህራኑ ጥያቄ ፍትሀዊ መልስ እንዲሰጥ የጠየቀ ቢሆንም ከዚህ በታች ስማቸው የተሰረዘው 109 መምህራን ከመንግስት ሰራተኞች የአስተዳደር ህግ ውጭ ከስራ ተባረው ለከፋ ችግር ተጋልጠው እንደሚገኙ አመልክተዋል ።

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

ከምባታ ጠምባሮ ዞን የጠምባሮ ወረዳ ያለአግባብ ከስራ ቅጥሩ የተባረሩ መምህራን

| | ስም | ጾታ |
|---|---|---|
| 1. | መ/ር ዳንኤል ለዕላጎ | ወንድ |
| 2. | መ/ር አማኑኤል አጤቦ | ወንድ |
| 3. | መ/ር ሀንዴቦ ሃሌኖ | ወንድ |
| 4. | መ/ር ግርማ ሄራኖ | ወንድ |
| 5. | መ/ር መንግስቱ ማሴቦ | ወንድ |
| 6. | መ/ር ታምራት ሀይሌ | ወንድ |
| 7. | መ/ር ማርቆስ ጌንሳ | ወንድ |
| 8. | መ/ር በላይነህ ደቦጭ | ወንድ |
| 9. | መ/ር ሞገስ በለጠ | ወንድ |
| 10. | መ/ት ፀሐይነሽ ሻሜቦ | ሴት |
| 11. | መ/ር መኮንን በላይነህ | ወንድ |
| 12. | መ/ር ጌታቸው መኮንን | ወንድ |
| 13. | መ/ር እልፍነሽ ደጉኖ | ሴት |
| 14. | መ/ር ሰገስ በደቀ | ወንድ |
| 15. | መ/ር አማኑኤል ጉጃቦ | ወንድ |
| 16. | መ/ር ደሳለኝ ደምሴ | ወንድ |
| 17. | መ/ር ደምሴ ለማ | ወንድ |
| 18. | መ/ር አሰፋ ጀባሞ | ወንድ |
| 19. | መ/ር ጳውሎስ አቦኖ | ወንድ |
| 20. | መ/ት ደሳለች ደነቀ | ሴት |
| 21. | መ/ር ተሾመ ጋሴቦ | ወንድ |
| 22. | መ/ር ጌትነት ማርቆስ | ወንድ |
| 23. | መ/ር አሰፋ ማዴቦ | ወንድ |
| 24. | መ/ር ፈንታዬ ወ/ሚካኤል | ወንድ |
| 25. | መ/ር በየነች ለዕለጎ | ወንድ |
| 26. | መ/ር በቀለ ደምሴ | ወንድ |
| 27. | መ/ር መሰለ ወሌቦ | ወንድ |
| 28. | መ/ር በትሶ ፎሴ | ወንድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 29. | መ/ር | አብዩ አድማሱ | ወንድ |
| 30. | መ/ር | በለጠ አንጆሎ | ወንድ |
| 31. | መ/ር | ጌታቸው ማርቆስ | ወንድ |
| 32. | መ/ር | ደሳለኝ ዴበንቾ | ወንድ |
| 33. | መ/ር | አሰፋ አየለ | ወንድ |
| 34. | መ/ር | ተስፋሁን መኬቦ | ወንድ |
| 35. | መ/ር | ተስፋሁን ዶሌቦ | ወንድ |
| 36. | መ/ር | ብርጋ ሎለሞ | ወንድ |
| 37. | መ/ር | ጌታቸው እርሰዶ | ወንድ |
| 38. | መ/ር | አባይነህ አንሼቦ | ወንድ |
| 39. | መ/ር | ሽብሩ ሳደሞ | ወንድ |
| 40. | መ/ር | ተከተል ንጉሴ | ወንድ |
| 41. | መ/ር | ንጉሴ አማኑኤል | ወንድ |
| 42. | መ/ር | ታደሰ ፊልታሞ | ወንድ |
| 43. | መ/ር | ፀጋዬ አበራ | ወንድ |
| 44. | መ/ር | አክሊሉ ያዕቆብ | ወንድ |
| 45. | መ/ር | ማሙዬ ሀልሶ | ወንድ |
| 46. | መ/ር | ሽወነህ አበራ | ወንድ |
| 47. | መ/ር | ሲሳይ ከልታሞ | ወንድ |
| 48. | መ/ር | ታዬ መሐመድ | ወንድ |
| 49. | መ/ር | ጥበቡ ሊራንሶ | ወንድ |
| 50. | መ/ር | አበራ ደፈቆ | ወንድ |
| 51. | መ/ር | ኢብራሂም አበበ | ወንድ |
| 52. | መ/ር | ታደሰ ወራቆ | ወንድ |
| 53. | መ/ር | ተገኘ መኮንን | ወንድ |
| 54. | መ/ር | ዳንኤል ሄሌቦ | ወንድ |
| 55. | መ/ር | ነጋሽ በለጠ | ወንድ |
| 56. | መ/ር | ሀ/ማርያም ማስቦ | ወንድ |
| 57. | መ/ር | ጴጥሮስ ሀይባሎ | ወንድ |
| 58. | መ/ር | ዳንኤል ወንድሙ | ወንድ |
| 59. | መ/ር | ማርቆስ ሻማነ | ወንድ |



የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ Human Rights Council

| | | | |
|---|---|---|---|
| 60. | መ/ር | አልማዝ ታረቀኝ | ወንድ |
| 61. | መ/ር | ታረቀኝ ዩሐንስ | ወንድ |
| 62. | መ/ር | መለሰ ዘለቀ | ወንድ |
| 63. | መ/ር | አልማዝ ሀይሌ | ወንድ |
| 64. | መ/ር | ሙሉጌታ ሃሴኖ | ወንድ |
| 65. | መ/ር | አማኑኤል ሻንኮሮ | ወንድ |
| 66. | መ/ት | አስቴር ሰላ | ሴት |
| 67. | መ/ር | ትዕግስት ከበደ | ወንድ |
| 68. | መ/ር | ፀጋነሽ ብርሃኑ | ወንድ |
| 69. | መ/ር | ቦጋለ ቀልቦሬ | ወንድ |
| 70. | መ/ር | ዘካሪያስ ኢሳያስ | ወንድ |
| 71. | መ/ት | አስቴር አዛዥ | ሴት |
| 72. | መ/ር | አብርሃም ተሰማ | ወንድ |
| 73. | መ/ር | አበጀ ቢልጥቦ | ወንድ |
| 74. | መ/ር | ተስፋዬ ታዲዮስ | ወንድ |
| 75. | መ/ር | ሙሉጌታ አልክሶ | ወንድ |
| 76. | መ/ት | እቴነሽ አልክሶ | ሴት |
| 77. | መ/ት | ሙሉ ብራሞ | ሴት |
| 78. | መ/ር | ማቴዎስ እሎ | ወንድ |
| 79. | መ/ር | ክብሩ ጳውሎስ | ወንድ |
| 80. | መ/ር | እዩኤል ጴጥሮስ | ወንድ |
| 81. | መ/ር | አዳነ ባቢሶ | ወንድ |
| 82. | መ/ር | ተመስግን ገ/ማርያም | ወንድ |
| 83. | መ/ር | ሞገስ ቦቶሬ | ወንድ |
| 84. | መ/ር | ማቴዎስ በቀለ | ወንድ |
| 85. | መ/ር | ሙሉጌታ ፋንታዮ | ወንድ |
| 86. | መ/ር | ዴቴቦ ዎገሶ | ወንድ |
| 87. | መ/ር | ሙሉጌታ ባርዲሎ | ወንድ |
| 88. | መ/ር | ተስፋዮ ሶሮሞ | ወንድ |
| 89. | መ/ር | ማቴዎስ መንገሻ | ወንድ |
| 90. | መ/ር | ታደሰ ደመቀ | ወንድ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 91. | መ/ር | ተስፋዮ ደስታ | ወንድ |
| 92. | መ/ር | ሌጌቦ ጃረና | ወንድ |
| 93. | መ/ር | ተሻለ ግርማ | ወንድ |
| 94. | መ/ት | ብዙነሽ ወንድሙ | ሴት |
| 95. | መ/ር | ሀይሌ ተሾመ | ወንድ |
| 96. | መ/ር | ደምሴ በቀለ | ወንድ |
| 97. | መ/ት | ጥሩነሽ ቡምቤ | ሴት |
| 98. | መ/ር | ፋንታዮ ወጭሬ | ወንድ |
| 99. | መ/ር | ሰላሙ አበራ | ወንድ |
| 100. | መ/ር | ታዴዎስ ታደሰ | ወንድ |
| 101. | መ/ር | ምስጋና በየነ | ወንድ |
| 102. | መ/ት | ደመቀች ገ/ዮሀንስ | ሴት |
| 103. | መ/ት | አስቴር በየነ | ሴት |
| 104. | መ/ት | አዳነች ቡሩሴ | ሴት |
| 105. | መ/ር | ተስፋዮ ታደሰ | ወንድ |
| 106. | መ/ት | አስቴር ሰላሙ | ሴት |
| 107. | መ/ር | ማቴዎስ መሸሻ | ወንድ |
| 108. | መ/ር | ማሞ አበበ | ወንድ |
| 109. | መ/ር | አብርሀም ተሰማ | ወንድ |

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

# ማጠቃለያ

በዚህ የሰመጉ 34ኛ መደበኛ መግለጫ የተመዘገቡት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የተመሰረቱት ጉዳዩ በተመለከታቸው ግለሰቦች በቀረቡ አቤቱታዎች እና ሰመጉ በሰበሰባቸው መረጃዎች ላይ ነው። ከዚህ መግለጫ መረዳት እንደሚቻለው የሀገራችን የሰብአዊ መብት ሁኔታ አሁንም ትኩረት ያሻዋል። ሕገ ወጥ ግድያ፣ ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝ መታሰር እና በቁጥጥር ስር የዋሉ ግለሰቦች ኢሰብአዊ አያያዝ፣ የስራ ዋስትና ማጣት አሳሳቢ ችግሮች ናቸው። ስለሆነም መንግስትና ልዩ ልዩ አካላት ሰብአዊ መብቶችን እንዲያስከብሩ እና ለመብቶች የተጠናከረ ሕጋዊና ተቋማዊ ጥበቃ እንዲያደርጉ ሰመጉ ይጠይቃል ። በተለይም፡-

- መንግስት ለሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ትኩረት በመስጠት ጥሰቶቹን የፈጸሙ ሁሉ ህግ ፊት እንዲቀርቡ እንዲያደርግ፣

- ከህግ ውጪ ለተገደሉ ዜጎች ቤተሰቦች፣ ለተደበደቡና ለቆሰሉ፣ እንዲሁም ለህገ ወጥ እስራት ለተዳረጉና ንብረታቸው ያለአግባብ ለወደመባቸው ሁሉ ተገቢው ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ እንዲመቻች፣

በመጨረሻም ዜጎችና ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ለህግ የበላይነት መስፈን የቆማችሁ ብሔራዊና ዓለም ዐቀፍ ድርጅቶች፣ መንግስት ለሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊውን የህግና የተቋማት ዝግጅቶች እንዲያደርግና ለትክክለኛ ተግባራዊነታቸውም በቂ ትኩረት እንዲሰጥ ከዚህ በታች ለተጠቀሱት የመንግስት አካላት በመጻፍ እንድታሳስቡ ሰመጉ ጥሪውን ያስተላልፋል።

- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈ ጉባኤ ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0900 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 80001፣ ፋክስ (251-11) 155 0722 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 1031፣ፋክስ (251-11) 155 2020 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 1031፣ ፋክስ (251-11) 155 2020 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0000 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትህ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0874 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 101769፣ ፋክስ (251-11) 551 3642 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
Human Rights Council

ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 18፣ፋክስ (251-46) 220 1950 ሐዋሳ ኢትዮጵያ

- የአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 312፣ ፋክስ (251-1) 058 220 1068 ስልክ (251-1) 058 220 2252 ባሕር ዳር፣ ኢትዮጵያ

- የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 44፣ ፋክስ (251-46) 2201950 አሶሳ

- የሶማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ፋክስ (251-25) 7753429 ጅጅጋ፣ ኢትዮጵያ

- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁጥር 199፣ ፋክስ (251-1) 153 4253 ስልክ (251-1) 551 2744 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ፖ.ሳ.ቁጥር 1165፣ ፋክስ (251-11) 6180040 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ፖ.ሳ.ቁጥር 2459፣ ፋክስ (251-11) 553 2053 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ